# አምባሳደር ዶን ያማሞቶና ቪኪ ሃድልስተን ስለኢትዮጵያ ምን አሉ?

**ሳሙኤል ፍስሃ - ከአዲስ አበባ**

ሰሞኑን ዊክሊክስ በአዲስ አበባ የሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ ዲፕሎማቶች ከኢትዮጵያ መንግሥት ባለስልጣናት ጋር ያደረጉትን ውይይትና በየግላቸው የያዙትን ስሜትና ግንዛቤ የሚያመላክቱ የደብዳቤ ልውውጦች ይፋ አድርጓል፡፡ እንደማንኛውም የአገሩ ጉዳይ የሚያሳስበው ሰው የአምባሳደሮቹን ደብዳቤዎች አንድ በአንድ ለመመልከት ሞክሬያለሁ፡፡ ከደብዳቤዎቹ የኢትዮጵያ መንግሥት በአሜሪካ ዲፕሎማቶች ዓይን እንዴት እንደሚታይ ለመገንዘብም ሞክሬያለሁ፡፡ ፈረንጆች curiosity killed the cat እንደሚሉት በጉዳዩ ላይ የተፃፉትን ሁሉ ልቅም አድርጌ ከተመለከትኩ በኋላ የተገነዘብኩት ግን የተመኘሁት ቀርቶ ያልተመኘሁትን ያገኘሁበት ነበር፡፡ በሌሎች ጉዳዮች ላይ ሌላ ጊዜ እንደምመለስበት በመተማመን ለዛሬው በአምባሳደር ዶን ያማሞቶና በሚስ ቪኪ አማካኝነት ከተላለፉት መልዕክቶች በመነሳት የተገነዘብኩትን ለአንባቢዎች ማካፈል መርጫለሁ፡፡

በቅድሚያ አምባሳደር ያማሞቶ ካነሷቸው ነጥቦች መጀመር ሳይሻል አይቀርም፡፡ ያማሞቶ የፃፉትን ደብዳቤ ስመለከት በመጀመሪያ የተገነዘብኩት በነሐሴ ወር 2000 ዓ.ም ላይ እጅግ በጣም ተናደው በኬብል ባስተላለፉት መልዕክት ፡-

> *«እኛ ለኢትዮጵያ መንግሥት ከፍተኛ ባለስልጣናት በኢትዮጵያና በአሜሪካ መካከል ያለው ስትራተጂያዊ አጋርነት አፀፋ መመለስን የሚጠይቅ እንደሆነና ለአሜሪካ መንግሥት ፀረ አሸባሪነት ትግል በባዶ ሆዋ የሚካሄድ እንዳልሆነ እናሳውቃቸዋለን፡፡ .... ለኢትዮጵያ መንግሥት ከምንሰጠው ያልተቆጠበ ድጋፍ ጋር ተያይዞ በአሜሪካ መንግሥት ጥቅሞች ላይ የሚያንዣብበው የረጅም ጊዜ አደጋ ከዚህም ጋር ተያይዞ የምንሰጠው የእርዳታ ፕሮግራም ደረጃና ስፋቱን እንደገና ልንመረምር እንገደድ ይሆናል» ማለታቸውን ነው፡፡*

አምባሳደር ያማሞቶ ኢትዮጵያ ለአሜሪካ በጎ ስራዎች አፀፋ እንዳልመለሰች አድርገው በመውሰድ እልህ በተሞላበት ሁኔታ የእርዳታ ፕሮግራማቸውን ወርድና ስፋት

እንደገና እንመረምራለን ያሉበት ምክንያት ደግሞ ዊክሊክስ ላይ በአስራ ሰባት ነጥቦች ተዘርዝሮ ተቀምጧል። የመጀመሪያው ወንጀል በምርጫ 97 የአይአርአይና (International Republican Institute) ኤንዲአይ (National Democratic Institute) እንዲሁም አይኤፍኢኤስ (International Foundation for Electoral Systems) አባላትን ማባረሯ፣ ይህም ከሃያ ዓመት ወዲህ በማንም አገር ያልተደረገና የኢትዮጵያ መንግሥት እንደገና እንዲመለሱ ቢጠየቅም ፈቃደኛነትን አለማሳየቱ የጥፋቱ ሁሉ አቡጊዳ ተደርጎ ቀርቧል። ምርጫ ቦርድ የ1.3ሚሊዮን ዶላር እርዳታ ተቀብሎ እያለ ለ2000 የቀበሌ ምርጫ ታዛቢዎችን አልፈቅድም ማለቱ፣ የገዢው ፓርቲ ኃላፊዎች በ99ዓ.ም ክረምት የቀረበላቸውን የፈቃደኛ ነብኚዎች ፕሮግራም ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆናቸው፣ መከላከያ ሚኒስቴር ከተሰጡት 41 የስልጠና ድጋፍ እድሎች 29ኙን አልቀበልም ማለቱ፣ በዚህ ሳይወሰን የስፔሻል ኦፐሬሽን ኃይሎች ስልጠናና ልዩ ልዩ ሴሚናሮችንም አሻፈረኝ ማለቱ፣ እንዲሁም የCombined Joint Task Force- Horn of Africa (GJTF-HoA) እንዳይካሄድ መከልከሉና የአሜሪካንን የፀረ ሽብርና የወሰን ፀጥታ አሰልጣኞችን ከብላቴ ማባረሩ ከ17ቱ ምክንያቶች ጥቂቶቹ ናቸው። እንደገናም የኢትዮጵያ መንግሥት የአሜሪካን የንግድ ምክር ቤትን ላለመመዝገብና ስራ እንዳይጀምር ለማድረግ ከዓመት በላይ ደጅ ማስጠናቱንና የዩኤስኤይድ ተባባሪ የፕሮግራም አስፈፃሚ የሆኑትን የWomen's Consent International (WCI) እና የAmerican Bar Association (ABA) አልመዘግብም ማለቱን በመጥቀስ አምባሳደር ያማሞቶ አሜሪካ ለሚገኙ ኃላፊዎቻቸው፡-

> *«የአሜሪካን መንግሥት ባለፈው ዓመት ኢትዮጵያ «ያልተከበሩ ቃልኪዳኖች» ስትላቸው የነበሩትን ሁሉ ለኢትዮጵያ ፀጥታና ፀረ አሸባሪነት ትግል ሲል እንዳከበረ ማሳየት ይገባናል። ይሁንና የኢትዮጵያ መንግሥት ያለማቋረጥ አሜሪካ ያሏትን አሳሳቢ ጉዳዮች በተለይም ደግሞ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሪፎርም እንዲካሄድና ትምምንን ለማጎልበት የነደፈችውን ፕሮግራም ማደናቀፉን መነሻ በማድረግ የአሜሪካ መንግሥት ከኢትዮጵያ ባለስልጣናት ጋር ሲነጋገር የቅኝት ለውጥ ማድረግ ይኖርበታል» ብለዋል።*

አምባሳደሩ አገራቸው ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ግንኙነት እንደገና ለመመርመር እንገደዳለን ለማለት የደረሱት በእነዚህ ምክንያቶች ነው። በሌላ በኩል እኝሁ አምባሳደር ኢትዮጵያ ውስጥ በነበሩበት ጊዜ በ2001 ዓ.ም ከጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ጋር ባደረጉት ውይይት መከላከያ ሰራዊቱ ጠይቆና እንዳይሰጠው ተከልክሎ የቆየውን

በጨለማ መመልከቻ የጦር ሜዳ መነፅር ችግር እንደፈቱና ኢትዮጵያ በሰብዓዊ መብት ሪፖርታቸው ላይ ባቀረበችው ቅሬታ ላይ ተመስርተው በመወያየት ችግሩን ለማስተካከል ዝግጁ እንደሆኑ ከገለፁ በኋላ፦

*«እርግጥ ነው አቶ መለስ ከአሜሪካ ጋር የተሻለ ግንኙነት መመስረት ይፈልጋሉ። ይህም ሲሆን ኢትዮጵያ በራሷ ፖሊሲዎች ላይ ተመስርታ የሰብዓዊ መብት፣ ዴሞክራሲና የኢኮኖሚ ልማትን ባራመደች ቁጥር አሜሪካ በራሳቸው ቅድመ ሁኔታ ላይ ተመስርታ ለኢትዮጵያ በቂ ምህዳር እንድትሰጥ በመፈለግ ጭምር የሚገለፅ ነው» ይላሉ።*

እስካሁን ካነበብኩት ለመረዳት እንደቻልኩት የኢትዮጵያ መንግሥት ባለስልጣናት አሜሪካኖቹን በልዩ ልዩ ጉዳዮች ሲያስቆጧቸውና ሲያበሳጯቸው እንደከረሙ ነው። ይህን 17 ጉዳዮችን ዘርዝሮ የኢትዮጵያ መንግሥት የአሜሪካንን ትዕዛዝና መመሪያ የማይቀበል እንደሆነ ዊክሊክስ አምባሳደር ያማሞቶን ዋቢ አድርጎ ካተመው ፅሑፍ ለመገንዘብ ችያለሁ። በብሔራዊ ጥቅሙ የመጣበትን የማንኛውንም አገር መመሪያ ብቻ ሳይሆን በዓለም ላይ የሃያሏን አገር መመሪያ አልቀበልም የሚል መንግሥት ምን ያህል በራሱና በኢትዮጵያ ህዝብ የሚተማመን እንደሆነ ያሳያል። የኢህአዴግን መሪዎች አቋም ድሮ በደርግ ጊዜ ዓለም በምስራቅና በምዕራብ ጎራ ተከፋፍላ በነበረችበትና ምስራቁ ባዘጋጀው የስፖርት ውድድር ላይ ምዕራቡ የማይሳተፍበት፣ ምዕራቡ ባዘጋጀው ደግሞ ምስራቁ የማይሳተፍበትና ኢትዮጵያ የሩሲያን መመሪያ ተቀብላ ከሴኡል ኦሎምፒክ እራሷን እስከ ማግለል የደረሰችበትን የተላላኪነት ዘመን ታሪክ ሳስታውስ በአሁኑ ዘመን አገሪቱ የውጭ ጌታ የሌላት ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

አምባሳደር ያማሞቶ በኢትዮጵያ የስራ ዘመናቸው ወደማብቃቱ ገደማ ከጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ጋር ከተገናኙ በኋላ የሰጡት አስተያየት ደግሞ የሚገርም መተጣጠፍ ያሳዩበት ነበር። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በግልፅ እንግሊዝኛ የምዕራቡን የዴሞክራሲ ፓራዳይም በአፍሪካ ላይ መጫን እንደማይገባ መንግሥታቸው በአፍሪካ አገር በቀል ዴሞክራሲ እንዲያብብ እንጂ ከውጭ በተፅዕኖ የሚጋት ዴሞክራሲ እንደማይቀበል መግለፃቸውን ተከትሎ ያማሞቶ እንዲህ ይላሉ፦

*«ጠቅላይ ሚኒስትሩ የአገዛዝ ስርዓትን በሌሎች አገሮች ላይ መጫን የለባችሁም በማለት ያቀረቡትን መከራከሪያ ከመቀበል በተጨማሪ በሁለቱ*

*አገሮች መካከል ያለውን ጥልቅ ልዩነት በትክክል መገንዘብና ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ያለንን መስተጋብር በትክክል በመቃኘት በዚህ አደገኛ ሪጅን ውስጥ የአሜሪካንን ጥቅም እንዴት ማራመድ እንዳለብን በጥንቃቄ ማሰብ ይኖርብናል» ይላሉ፡፡*

ያማሞቶ ከቁጣቸው በረድ ብለው ሲያስቡ መንግሥታቸው የኢትዮጵያን መንግሥት እጅ በመጠምዘዝና የፈለገውን በማስፈፀም ሳይሆን በመመካከር መሄድ እንዳለበት ወደማሳሰብ ማምራታቸው የኢትዮጵያ መንግሥት ትዕግስትና ለእምነቱ ሟችነት የማታ ማታ ፍሬ እንዳስገኘ የሚያመላክት ነው፡፡

የያማሞቶን በድንፋታ ጀምሮ እየሰከነ የሄደ ፖለቲካ እዚህ ላይ ገትተን ወደ አምባሳደር ቪኪ ደግሞ ስንሄድ በጣም የተለየ አስተዋይነት እንመለከታለን፡፡ ቪኪ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩት በውጥረቱ ዘመን ነው፡፡ ከአምባሳደር ኦሪሊያ መሄድ በኋላ ከ97 መጨረሻ እስከ 99 መጀመሪያ በኢትዮጵያ ያገለገሉት ቪኪ ስራቸውን ጨርሰው ኃላፊነቱን ለአምባሳደር ያማሞቶ ሲያስረክቡ ወደ አገራቸው ባስተላለፉት መልዕክት እንዲህ ይላሉ፡-

*«ኃላፊነቴን ለመልካሙ ጓደኛዬና የተከበረው የስራ ባልደረባዬ አምባሳደር ዶን ያማሞቶ ሳስረክብ የአሜሪካንን መንግሥት ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን ግንኙነትና አጋርነት እንዲያጠብቅና እንዲያጠናክር እጠይቃለሁ፡፡ ኢትዮጵያ በትክክለኛው አቅጣጫ ወደፊት በመራመድ ላይ ነች፡፡ ምንም እንኳን ኢትዮጵያ አይሳካላትም የሚሉ ቢኖሩም አገሪቱ ዴሞክራሲና እድገትን እንዲሁም ቀጠናውን ከአሸባሪነትና አክራሪነት በመጠበቅ አኳያ የተዋጣለት ስራ እየሰራች ነች፡፡»*

አምባሳደር ቪኪ እንደገና ሁኔታውን በቅርቡ ከተከታተሉ በኋላ በተለያዩ ደብዳቤዎች ላይ እንዲህ ይላሉ፡-

*«ከጠቅላይ ሚኒስትሩና የቅርብ ጓዶቻቸው ጋር እንዲሁም ከተቃዋሚዎች ጋር የትምምን ግንኙነት ስለፈጠርን ፓርላማው ህጎቹን እንዲያሻሽልና በፓርላማ ውስጥ ሙግት እንዲቀሰቀስ ጠቃሚ ሚና ተጫውተናል፡፡ ገዢውም ፓርቲ ከህጋዊ ተቃዋሚዎች ጋር ድርድር ቀጥሏል፡፡ ከእነርሱ ጋር በመስማማትም አዲስ የምርጫ ቦርድ ለመሰየም ተዘጋጅቷል፡፡ ፓርላማው ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ የፀረ አሸባሪነትና የሚዲያ ህጎች*

*ለማውጣት እየተዘጋጀ ነው። በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊው አዝማሚያ አወንታዊ ሆኖ ይገኛል። በዚህ ወቅት በአገራችን ኢትዮጵያን ከአሸባሪ አገሮች ጋር እኩል የሚያሰልፍ ህግ ለማውጣት ጥረቱ ከቀጠለ አጋርነቱ ለአደጋ መጋለጡ አይቀርም » ይላሉ።*

ቪኪ በዚህ ሳይወሰኑ ከአቶ መለስና ከኢህአዴግ ባለስልጣናት ጋር ያካሄድነው ውይይት መሪዎቹ ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲና እድገት ያላቸውን ቁርጠኝነት ይበልጥ የሚያጠናክር ሆኖ አግኝቼዋለሁ ይላሉ። ቪኪ በኢህአዴግና በተቃዋሚዎች መካከል የተካሄዱ ውይይቶች በርካታ ጠቃሚ ውጤቶች እንዳስገኙ፤ የፓርላማን ህግ፣ የሚዲያ ህግን፣ የፓርቲዎችን የገንዘብ ድጎማ በድርድር እንደወሰኑ ካስቀመጡ በኋላ፡-

*«ሂደቱን በቅርብ ለተመለከተ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዴሞክራሲን ለማስፈንና ድህነትን ለማስወገድ ያላቸውን ቁርጠኝነት በይፋ መግለፃቸው የላቀ ጥቅም ያለው ሆኖ ይገኛል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዘጠኝ ወራት ውስጥ በፓርላማ ፊት ስድስት ጊዜ ቀርበዋል። የተቃዋሚዎች አስተያየቶችና ትችቶች በቴሌቪዥንና በመንግሥት ፕሬሶች ተስተጋብተዋል። ገዢው ፓርቲ በቅርቡ ባካሄደው ስብሰባው የመልካም አስተዳደር ችግር እንዳለበት አምኖ በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት ይህንኑ ለማሻሻል እንደሚፈልግ መግለፁም ትልቅ እርምጃ ነው» ብለዋል።*

በተጨማሪም ቪኪ «ዴሞክራሲያዊ ሂደት አወንታዊ ነው። ነገር ግን በእኛ በኩል ኢትዮጵያን በአሸባሪነት ዝርዝራችን ውስጥ ከያዝናቸው አገሮች ጋር እኩል የሚያሰልፍ ህግ ለማውጣት ለሚካሄዱብን ጫናዎች ካጎበደድን አጋርነታችን ሊጠናከር አይችልም። ....... ኢትዮጵያን እንደተመለከትኳት ከሆነ መቼም ቢሆን ከደካማነት ወይም በእርሷ ላይ ከሚካሄድ ግልፅ ዛቻ ወይም እርዳታን እናቋርጣለን ከሚል ማስፈራሪያ በመነሳት ማንበርከክ አይቻልም። በሌላ በኩል ግን ኢትዮጵያ ወዳጆቿን ትሰማለች ስትሰማም ኖራለም» ብለዋል።

ቪኪ ይህን ካሉ በኋላ የኢትዮጵያን መንግሥት ለማሳመን ጥቅም ላይ መዋል ስላለባቸውና ስለሌለባቸው መንገዶች ሲያነሱ በተለያዩ ቦታዎች ላይ የሚከተሉትን ሃሳቦች ያስቀምጣሉ።

*«እኛው እራሳችን ለኢትዮጵያ ያለንን ወገናዊነት ለማጠናከር ቁርጠኝነቱ ካለን በእጅጉ እንጠቀማለን። ነገር ግን ዲያስፖራውን ወይም አንዳንድ*

*የአሜሪካን ኮንግረስ አባላትንና የሲቪል ሶሳይቲ ኃይሎችን ለማስደሰት ብለን በአቶ መለስ መንግሥት ላይ ግፊት ካበዛንና አጠራቃቂ አቅጣጫ ከተከተልን ኢትዮጵያን ማጣታችን አይቀርም። በኢትዮጵያ ላይ ሊኖረን የሚችለውን በጎ ተፅዕኖ የማሳረፍ እድል የመድበለ ፓርቲ ስርዓት ብዙም ለማያስጨንቃቸው እንደ ቻይና፣ ሩሲያ ለመሳሰሉ ሌሎች አገሮች አሳልፈን እንሰጣለን» ይላሉ።*

ስለጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በሚገለፁበት ቦታም ላይ

*«አቶ መለስ ሁሌም ቢሆን የእኛን ጥያቄዎች ከማስተናገድ ይልቅ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም አስፈላጊ ነው ያለውን ነገር ያደርጋል» እናም አቶ መለስ በአክብሮትና በአጋርነት መንፈስ ካልቀረብነው በስተቀር የፈለግነውን ምላሽ አይሰጠንም። ዛሬ ከአቶ መለስና ከኢህአዴግ ከፍተኛ የአመራር ማዕከል ጋር መሰላቸው ያለበትም ቢሆን መልካም ግንኙነት ፈጥረናል። ግንኙነቱ ዛሬም ቢሆን በደንብ አልጠነከረም። ይህም የሆነው ዋሽንግተን ኢትዮጵያን በማሻሻል ላይ ባለችው የሰብዓዊ መብት አያያዝ የሚዋልል አቋም ስላላት ነው ይላሉ።*

ቪኪ በዚህ ብቻ ሳይወሰኑ «የኢትዮጵያ መንግሥት ምንም እንኳን ወዳጅ አድርጎ የሚቆጥረን ቢሆንም በተለይ ማዕበል ሲነሳ መካካዱ የሚበዛ ከሆነበት ከምዕራቡ ዓለም ጋር ግንኙነቱን እንደገና ለማደስ ጊዜና ጉልበት ማባከንን እንደ ጠቃሚ ጉዳይ ላይወስደው የሚችልበት እድል ይኖራል። በተጨባጭ እንደሚታየው አቶ መለስ ከአውሮፓ ጋር ያላቸው የትብብር ግንኙነት ከቀውሱ በኋላ ቢሻሻልም ከሞላ ጎደል ፊታቸውን ይበልጥ አስተማማኝ ወደሆነችው ቻይና አዙረዋል» በማለት ጫናና ግዳጅ የበዛበትን ግንኙነት እንደማይደግፉ በደብዳቤያቸው አስታውቀዋል።

በአምባሳደር ቪኪና በአምባሳደር ዶን ያማሞቶ ደብዳቤዎች የኢትዮጵያ መንግሥት ጌታ የለሽና ከኢትዮጵያ ጥቅሞች በስተቀር ለማንም እጁን የማይሰጥ መንግሥት እንደሆነ አሳይቷል። መንግሥት በየእለቱ ከአሜሪካኖች ጋር የገባባቸውን አተካራዎች ባይነግረንም ከሪፖርቱ በብዙ ጉዳዮች ላይ እየተሟገተና የማይቀበለውን አልቀበልም እያለ እንደተጓዘ አሳይቷል። የአሜሪካን ዲፕሎማቶች ደግሞ ሁለት አይነት መሆናቸውን በዊኪሊክስ ሪፖርት ታዝበናል። አንዳንዶቹ ሲጀምሩ በሸሮ ድንፋታ ጀምረው በሂደት የሚበርዱ፣ ሌሎቹ ደግሞ ከመጀመሪያው አርቆ አስተዋይነት ያልተለያቸውና ለጋራ ጥቅምና ለመከባበር ቅድሚያ የሚሰጡ መሆናቸው ታይቷል።

ዲፕሎማሲ በአገሮች መካከል የጋራ ጥቅሞችን በማስፋትና ወዳጅ በማበራከት ብሔራዊ ጥቅምን የማረጋገጥ ስራ በመሆኑ ቪኪ ሃድልሰንና የኢትዮጵያ መንግሥት ባለስልጣናት ቀናውን ጎዳና ይዘው መጓዛቸውን እድሜ ለዊኪሊክስ መታዘብ ችያለሁ።

በፅሑፌ ማጠቃለያ ላይ የኢትዮጵያ መንግሥት ኃላፊዎች አሜሪካንን ከሚያክል አገር ጋር ባላቸው ግንኙነት «ሲጠሩት አቤት ሲልኩት ወዴት» አይነት ተላላኪዎች አለመሆናቸውን ዊኪሊክስ በለቀቃቸው ደብዳቤዎች ለመታዘብ ችያለሁ። እኔ የኢትዮጵያ መንግሥት ብሆን ኖሮ ይህን የሶስተኛ ወገን ነፃ ምስክርነት እያባዛሁ ለአንባቢያን ሁሉ በሰጠሁ ነበር። ዳሩ ምን ያደርጋል የኢትዮጵያ መንግሥት ከመናገር ይልቅ ሞያ በልብ ነው ብሎ የሚያምን ይመስላል። ለዛሬው በዚሁ እንሰናበታለን።